# የክርስቲያን – ሙስሊም ውይይት

በዶክተር እውነቱ

አዲስ አበባ
1991 ዓ.ም.

# የክርስቲያን –ሙስሊም ውይይት

ዶክተር እውነቱ፡- በሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መካከል ብዙ የአሳብ ልዩነቶች ስላሉ ይህን የመወያያ ጊዜ ማግኘታችን ደስ ብሎኛል። ከዚህም ውይይት የተነሣ ወደፊት የተሻለ መግባባት እንዲኖረን ምኞቴ ነው።

አህመድ፡- እምነቴን ለክርስቲያኖች የማካፍልበትን ዕድል ሁልጊዜም በደስታ እቀበላለሁ፤ አሁን ግን አንተ ስለምታምነው ነገር ብትነግረኝ ለመስማት ፈቃደኛ ነኝ።

እውነቱ፡- ዋናው ነገር እኔ በአንድ አምላክ ማመኔ ነው።

አህመድ፡- እውነትህን ነው? ይህን ከዚህ በፊት በጭራሽ ሰምቼ አላውቅም! ክርስቲያኖች በሦስት አማልክት የሚያምኑ ይመስለኝ ነበር!

እውነቱ፡- እኛ በሦስት አማልክት አናምንም፤ ይኼማ የማይሆን ነገር ነው። እንዴት ሦስት አማልክት ሊኖሩ ይችላሉ? ክርስቲያኖች ብሉይና አዲስ ኪዳንን ይቀበላሉ፤ ሁለቱም ደግሞ በግልጽ፥ «አምላካችን እግዚአብሔር አንድ ነው» በማለት ያስተምራሉ (ዘዳግም 6፡4፤ ማርቆስ 12፡29)።

ስለሆነም፥ እንደ አይሁዶችና ሙስሊሞች እኛም የምናምነው በአንድ አምላክ ነው።

አህመድ፡- እኔ ብሉይ ኪዳን ለአይሁዶች፥ አዲስ ኪዳን ደግሞ ለክርስቲያኖች የተጻፈ ይመስለኝ ነበር።

እውነቱ፡- እንዲያውም የኢየሱስ ሐዋርያትና የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በሙሉ አይሁዶች ነበሩ።

አህመድ፡- እውነት ነው...እኔ ግን እንደዚህ አስቤም አላውቅም፤ ብዙዎቹ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች አይሁዶች ነበሩ።

እውነቱ፡- በመሆኑም፥ አይሁዶች በዕብራይስጥ የተጻፉትን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብቻ ሲቀበሉ፥ ክርስቲያኖች ግን ብሉይና አዲስ ኪዳንን ይቀበላሉ፤ እነዚህም ሁለቱ ጎን ለጎን የሚሄዱና እንደ ተመለከትነው እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ናቸው።

ይሁንና፥ ከዚሁ በአንድ አምላክ ላይ ስለሚኖር እምነት ጉዳይ ሳንወጣ በፊት፥ ክርስቲያኖች ከእናንተው ሻዳ ጋር የሚመሳሰል የእምነት መግለጫ እንዳላቸው ታውቃለህ? በዚህ የእምነት መግለጫቸው ውስጥ ክርስቲያኖች የሚናገሩት የመጀመሪያው ነገር «ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በአንድ አምላክ አምናለሁ» የሚል ነው።

አህመድ፡- ስለ እምነት መግለጫችሁ ሰምቻለሁ፤ ከእነዚህም መካከል አንዱ የኒቂያ የእምነት መግለጫ የምትሉት ነው፥ አይደል?

እውነቱ፡- ልክ ነህ። ይህ የእምነት መግለጫ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አጠቃላይ ተቀባይነት ያገኘው በኒቂያ ጉባኤ እንደ ክርስቲያኖች አቆጣጠር በ325 ዓመተ ምሕረት ነው።

አህመድ፡- ይህ እንግዲህ ከነቢዩ መሐመድ ልደት ሁለት መቶ ሃምሳ ዓመታት በፊት ነበር ማለት ነው።

እውነቱ፡- አዎ።

አህመድ፡- አሁን ክርስቲያኖች በሦስት አማልክት እንደምታምኑ ለምን እንዳሰብሁ ልትነግረኝ ትችላለህ። በሥላሴ ታምናላችሁ፥ አይደል? ይህ ደግሞ ሦስት አማልክት ማለት ነው፥ አይደል?

እውነቱ፡- እስኪ ስለ ሥላሴ ከመነጋገራችን በፊት ስለ ኢየሱስ እንነጋገር፤ ምክንያቱም ኢየሱስ በእስልምና ከታላላቅ ነቢያት እንደ አንዱ ሆኖ ተቆጥሯል፤ አይደል?

አህመድ፡- አዎ፤ ሙስሊሞች በከፍተኛ ደረጃ ያከብሩታል። እንዲያውም በቁርአን ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል እና መሢሕ ተብሏል (ሱረቱ 3፡45፤ 4፡171)።

እውነቱ፡- ያ በጣም ጥሩ ነው። ቁርአን ኢየሱስ ከድንግል ማርያም ያለ ሰብአዊ አባትና ያለ ምንም የፈቃደ-ሥጋ ግንኙነት እንደ ተወለደ ከሚናገረው የአዲስ ኪዳን አሳብ ጋር እንደሚስማማ አውቃለሁ። ይኼ እውነት ነው፥ አይደል?

አህመድ፡- ቁርአናችን የሚያስተምረው ይህንኑ ነው፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን እንደሚያስተምር አላውቅም ነበር። ኢየሱስ የተጸነሰው በአላህ ትእዛዝ እንደሆነ እናምናለን፤ አላህ «ኹን» አለው- ሆነም (ሱረቱ 3፡47)።

እውነቱ፡- በዚህ አሳብ ልንስማማ እንችላለን።

አህመድ:- እውነትህን ነው? እኔ ግን የሚመስለኝ ክርስቲያኖች ሥላሴ ብለው የሚያምኑት እግዚአብሔር ከማርያም ጋር የጋብቻ ዓይነት ግንኙነት እንደነበረውና የፊቃደ-ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም ኢየሱስን እንደ ወለዱ ነበር።

እውነቱ:- ቁርአን የክርስትናው ሥላሴ አብ፥ ወልድና ማርያም እንደሆኑ የሚጠቁም መሆኑን አውቃለሁ (ሱረቱ 5፡116)፤ ነገር ግን በማንኛውም ዘመን በዚህ ዓይነቱ ሥላሴ ያመነ ክርስቲያን አልነበረም። እንዲያውም የዚህ ዓይነቱን ሥላሴ የሚያመለክት መረጃ ከየትኛውም ስፍራና ጊዜ ልታቀርብልኝ ትችል እንደሆነ ልጠይቅህ እፈልጋለሁ። ደግሞም ማንም ክርስቲያን ማርያምን አምልኳት አያውቅም።

አህመድ:- የሮማ ካቶሊኮችና ኦርቶዶክሶች አያመልኳትም እንዴ?

እውነቱ:- የለም፥ አያመልኳትም። አንዳንድ ሙስሊሞች መሐመድና ሙስሊም ቅዱሳን ስለ እነርሱ አላህን እንዲያማልዱ እንደሚለምኑ ሁሉ፥ አንዳንድ ክርስቲያኖችም ማርያም እንድታማልድላቸው ይለምናሉ። ነገር ግን ማርያምን አያመልኳትም። ይህ ሙስሊሞች መሐመድን ቢያመልኩ የሚሆነውን ያህል ለክርስቲያኖች የከፋ ነገር ነው።

አህመድ:- አሃ እዚያ ላይ ተሳስቻለሁ ማለት ነው። እናንተ ግን ኢየሱስን ታመልካላችሁ፥ አይደል?

እውነቱ:- መልካም፥ እዚህ ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ለመጥቀስ እገደዳለሁ፤ አንተ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተበረዘ የምታምን መሆንህን አውቃለሁ፤ ይሁንና፥ ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ርዳታ ስለ ኢየሱስ ብዙ ልናውቅ አንችልም። ቁርአንም ቢሆን ስለ ኢየሱስ የሚነግረን በጣም ጥቂት ነው።

አህመድ:- አዎን፥ ይኼ እውነት ነው። ምንም እንኳ ቁርአን ስለ ኢየሱስ መወለድና ሞት እንዲሁም ደቀ መዛሙርት እንደነበሩት እና ተአምራትን እንዳደረገ ቢናገርና እኛም የክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተበረዘ ብናምንም፥ አሁን በዚሁ መጽሐፍ መጠቀም አለብን፤ አለዚያማ ስለ ክርስትና ልንነጋገር አንችልም ማለት ነው።

እውነቱ:- ይህ ከሆነ እንግዲህ ኢየሱስ ከፈጸማቸው ተአምራት መጀመሩ ጥሩ ይመስለኛል። ቁርአን ኢየሱስ የዕውሮችን

ዓይኖች እንደ ከፈተና ለምጻሞችን እንዳነጻ ይናገራል (ሱረቱ 3:49)። የአንድ ዓይነ-ስውር መፈወስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ተጽፎአል። ከተፈወሰ በኋላም፥ «ጌታ ሆይ፥ አምናለሁ አለ፤ ሰገደለትም» የሚል እናነባለን (ዮሐንስ 9:38)።

በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ሰውየው እንዳያመልከው ሊያስቆመው አልሞከረም ወይም እንዳይሰግድለት አልገሠጸውም። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ መጨረሻ አካባቢ በዮሐንስ ራእይ ውስጥ፥ አንድ መልአክ ከሐዋርያው ዮሐንስ ጋር ሲነጋገር እንመለከታለን። ዮሐንስ፥ «...በመልአኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ። እርሱም፦ እንዳታደርገው ተጠንቀቅ...ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ» ሲል ገልጾአል (ራእይ 22:8-9)።

ይህ ስለ መሢሑ ኢየሱስ ምን ያመለክታል?

አህመድ፦ ለዚህ ብዙ አማራጮች አሉት፤ የእናንተ መጽሐፍ የተሳሳተ ሊሆን ይችላል። ምናልባት ደግሞ ሰውዬው ኢየሱስን እንዳመለከው የሚናገረውን ቃል አንድ ሰው ጨምሮታል ወይም ኢየሱስ የሰጠውን ምላሽ ሳይመዘግብ አልፎአል። ነገር ግን ሰውዬው እውነት ኢየሱስን ካመለከና ኢየሱስም ሊከላከለው ካልሞከረ፥ እንግዲህ....

እውነቱ፦ እሺ?

አህመድ፦ ወይ ኢየሱስ እውነተኛ ነቢይ አይደለም ማለት ነው፤ እኔ ግን እውነተኛ ነቢይ መሆኑን አምናለሁ አልያም ኢየሱስ ከነቢይ በላይ ነበር ማለት ነው።

እውነቱ፦ አሁንም እስኪ በዮሐንስ ወንጌል ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ የተገለጸበትን ምንባብ እንመልከት። መጀመሪያ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገለጽ ቶማስ የተባለው ሐዋርያ በዚያ አልነበረም። ኢየሱስም በሌላው ቀን፥ «ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው። ቶማስም፦ ጌታ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው» (ዮሐንስ 20:27-29)። አሁንም ኢየሱስ ጌታዬና አምላኬ ብሎ ስለ ጠራው ቶማስን ለመከላከል ወይም ለመገሠጽ ሲሞክር አንመለከትም፤

ይልቁንም ይህንኑ እውነት የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው ብሏል።

አህመድ፡- ምንም እንኳ ከዚህ በፊት ይህንን ታሪክ ባላነበውም፥ አንድ ሰው ፈጥሮ ጨምሮት ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ኢየሱስ መሢሕና ‹የእግዚአብሔር ቃል› ነበር። እንዲሁም ደግሞ ማርያም ከተባለች ድንግል ሴት እንደ ተወለደ አምናለሁ። ግን ይኼ አምላክ ሊያደርገው አይችልም። አዳምም ቢሆን ሰብአዊ አባት ወይም እናት አልነበረውም፤ እርሱ ግን አምላክ አልነበረም፥ ነበር እንዴ?

እውነቱ፡- በዚህ ከአንተ ጋር እስማማለሁ። ኢየሱስ ከድንግል መወለዱ አምላክነቱን አያረጋግጥም፤ ነገር ግን ይህ ኢየሱስ ከሰው ፈቃድ ወይም ተግባር ውጭ ወደ ዓለም እንደ መጣ ያረጋግጣል። ኢየሱስን ወደ ዓለም ያመጣው የእግዚአብሔር ኃይል ነበር።

አህመድ፡- ግን ኢየሱስ ከነቢይ እንደሚበልጥ የሚያሳይ ሌላ መረጃ በእናንተ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ?

እውነቱ፡- እንዴታ፥ አለ። ኢየሱስ ተይዞ በታሰረ ጊዜ ምን አጥፍተሃል ተብሎ ነበር የተከሰሰው?

አህመድ፡- የፖለቲካ ዓማፂ ነህ ተብሎ ነዋ!

እውነቱ፡- ይኼማ በሕጋቸው አስቀድሞ የኮነኑት የአይሁድ መሪዎች ወደ ሮም ባለሥልጣናት ባመጡት ጊዜ ነበር። ቀድሞ አይሁዶች የከሰሱት ስለምን ነበር?

አህመድ፡- እኔ እንጃ።

እውነቱ፡- በእግዚአብሔር ላይ የስድብን ቃል ተናግሯል ተብሎ ነበር የተከሰሰው። የማርቆስ ወንጌል እንደሚለው፥ «ሊቀ ካህናቱም በመካከላቸው ተነሥቶ፡- አንዳች አትመልስምን? እነዚህስ በአንተ ላይ የሚመሰክሩብህ ምንድር ነው? ብሎ ኢየሱስን ጠየቀው። እርሱ ግን ዝም አለ አንዳችም አልመለሰም። ደግሞ ሊቀ ካህናቱ ጠየቀውና፡- የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን? አለው። ኢየሱስም፥ እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ አለ። ሊቀ ካህናቱም ልብሱን ቀደደና፡- ከእንግዲህ ወዲህ ምስክሮችን ምን ያስፈልገናል? ስድቡን ሰማችሁ...» (ማርቆስ 14:60–64)።

አህመድ፡- ግን እርሱ የተናገረው በእርግጥ የስድብ ቃል ነበር?

እውነቱ፡- ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ የሚያውቀው ማነው? ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ የምንኖርና አይሁዶች ያልሆንን እኛ ወይስ የሙሴን ሕግ የሚያውቁና ኢየሱስ የተናገረውን በገዛ ጆሮአቸው የሰሙ ካህናት? የሚሻለው ዳኛ ማን ሊሆን ይችላል?

አህመድ፡- እንደሚመስለኝ የተሻለ ብያኔ ሊሰጡ የሚችሉ የአይሁድ ካህናት ናቸው... ይህ ማለት ግን ኢየሱስ ከነቢይ እንደሚበልጥ የሚናገር መሆኑን ተረድተዋል ማለት ነው።

እውነቱ፡- ይህ ትክክል ነው። ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ትፈልጋለህ?

አህመድ፡- አዎ፥ ነገር ግን እኛ ሙስሊሞች የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን እንደማንቀበል በድጋሚ ልገልጽልህ እፈልጋለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተበረዘ እናምናለን። ምናልባት አንተ የጠቀስሃቸው ጥቅሶች በእናንተ በክርስቲያኖቹ የተጨመሩ ይሆናል።

እውነቱ፡- የምታምነው እንዲያ እንደሆነ ይገባኛል። አሁን ግን ከወንጌላት ሌላ ጥቅስ ላንብብልህ።

«በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» (ዮሐንስ 1፡1)። ሙስሊም እንደ መሆንህ፥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ታምናለህ፥ አይደል?

አህመድ፡- አዎ፥ ይህ በቁርአን ውስጥ የሚገኝ ነውና ማመን አለብኝ (ሱረቱ 3፡45፤ 4፡171)።

እውነቱ፡- መጽሐፍ ቅዱስም ከዚህ አሳብ ጋር ይስማማል፥ የእግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር እንደሆነም ይገልጻል።

አህመድ፡- ከዚህ በፊት ስለዚህ ጥቅስ ሰምቻለሁ፤ አንዳንድ ተርጓሚዎች በዚያ መልኩ እንደማይተረጉሙትም ተነግሮኛል። ይልቁንም ያ ቃል ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ወጣ ይናገራሉ። ምንም እንኳ እኔ የግሪክ ቋንቋ ባላውቅም፥ ይህንን ልዩነት ለማምጣት በአንዱ ፊደል ላይ ትንሽ ለውጥ ማድረግ ብቻ እንደሚበቃ ነው። ይህ ትክክል አይደለም?

እውነቱ፡- ትክክል ነው፤ በግሪክ ቋንቋ እግዚአብሔር (THEOS) ከሚለው ከእግዚአብሔር (THEOU) ወደሚል አሳብ ለመቀየር የሚያስፈልገው በመጨረሻዋ ፊደል ላይ ለውጥ ማድረግ ብቻ ነው። ነገር ግን ማንም ሰው ከ "THEOS" ወደ "THEOU" የተደረገ ለውጥ ያለበትን የዮሐንስን ወንጌል ጥንታዊ መዝገብ አላገኘም። በአንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ ያ ጥቅስ ሌላ ትርጉም እንዲሰጥ ተደርጎ መለወጡም እውነት ነው። «ኒው ዎርልድ ትራንስሌሽን» በሚባለው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ነው «ቃሉም አምላክ ነበረ» የሚል ትርጉም የምንመለከተው። «እግዚአብሔር» ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ተራ «አምላክ» ተብሎ ተተርጉሟል። ይህንን ያደረጉት ግን የኢየሱስን አምላክነት የማይቀበሉ የይሖዋ ምስክሮች ናቸው። ከትምህርታቸው ጋር ስለማይገጥም ያንን ጥቅስ ለመቀየር ተገደዱ።

አህመድ፡- ነገር ግን ማንም ሰው ከእምነቱ ጋር ይስማማ ዘንድ ቅዱሱን መጽሐፍ ሊለውጥ አይችልም፤ እምነቱን ከቅዱስ መጽሐፍ ጋር እንዲስማማ ማድረግ እንጂ።

እውነቱ፡- ግሩም አባባል ነው። ሰው ለቅዱስ መጽሐፍ መታዘዝ አለበት። እንደምትመለከተው ግን የመጀመሪያው ምእተ ዓመት ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ችግሮች ነበሩባቸው። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ሰዎች አምላክ ነህ ሲሉት በአዎንታ የተቀበለ ሲሆን፥ እርሱም ራሱ አምላክነቱን ገልጾአል። እንዲያውም በወንጌላት ውስጥ ኢየሱስ ስለ ራሱ የሚከተለውን ተናግሮ ይገኛል።

«እኔና አብ አንድ ነን። አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ። ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው። አይሁድም ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት» (ዮሐንስ 10፡30-33)።

አህመድ፡- አይሁዶች በመሆናቸው መቼም እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አጥብቀው ያምኑ ነበር። በእነርሱ አስተያየት ኢየሱስ እንዴት አምላክ ሊሆን ይችላል?

እውነቱ፡- እንግዲህ ችግሩ ያለው እዚህ ላይ ነው፤ ክርስቲያኖች አንድ አምላክ እንዳለ የሚያምኑ ሲሆን፥ ኢየሱስ ግን ሰዎች

እርሱን ከማምለክ አልፈው እግዚአብሔር ብለው እንዲጠሩትም ፈቅዷል።

አህመድ፡- የእናንተ የክርስቲያኖች ችግር ይታየኛል፤ ያ የሆነው ግን የእናንተው መጽሐፍ የተሳሳተ በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር አንድ እንጂ ሦስት አይደለም። ቁርአን ኢየሱስ ተአምራት እንደ ሠራ ከሚናገረው ከእናንተው መጽሐፍ አሳብ ጋር ይስማማል፥ ያ ግን ኢየሱስ አምላክ መሆኑን አያረጋግጥም፥ አይደለም?

እውነቱ፡- አያረጋግጥም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ኤልያስና ኤልሳዕ የመሳሰሉ ነቢያት፥ ብሎም ሐዋርያቱ ጳውሎስና ጴጥሮስ በእግዚአብሔር ኃይል ሙታንን አስነሥተዋል። እንዲያውም በሙሴ ዘመን በግብፅ የፈርዖን መተተኞች ተአምራትን አድርገዋል (ዘጸአት 7፡8-12)። ስለሆነም፥ ተአምራት በራሳቸው የኃይልን መኖር ከሚያሳዩት በቀር ኃይሉ የማን እንደሆነ ወይም ከየት እንደ መጣ የሚያመለክቱ አይደሉም።

አህመድ፡- በዚህ ነጥብ ላይ ከአንተ ጋር እስማማለሁ። በመሠረቱ መሐመድ ቁርአንን ለእኛ ከመስጠት በቀር ሌላ ተአምር አልሠራም።

እውነቱ፡- ውድ ወዳጄ፥ ስለ ቁርአን አንድ አስገራሚ ነገር ተመልክቻለሁ። ይኸውም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚመሳሰሉ ነገሮችን ልናገኝ መቻላችን ነው። እግዚአብሔር በሚናገርበት ጊዜ፥ «እኛ» የሚል እንጂ፥ «እኔ» የሚል ቃል አይጠቀምም። በእኛ መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት አንድ ስለ ፍጥረት በሚናገረው ታሪክ እግዚአብሔር «ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» ብሏል (ዘፍጥረት 1፡26)። ምንም እንኳ በቁርአን ውስጥ ይህንኑ የሚመስሉ ብዙ ምንባቦች ቢኖሩም፥ እስኪ አንዱን ብቻ እናንብብ።

«ይህ መጽሐፍ (ከአላህ ለመኾኑ) ጥርጥር የለበትም፤ ለፈራህያን መሪ ነው። ለነዚያ በሩቁ ነገር የሚያምኑ፥ ሶላትንም ደንቡን ጠብቀው የሚሰግዱ ከሰጠናቸውም ሲሳይ የሚቸሩ ለኾኑት» (ሱረቱ 2፡2-3)።

«እኛ» የሚለው ለምንድን ነው?

አህመድ፡- እግዚአብሔር ከታላቅነቱ የተነሣ እንደዚያ ይናገራል፤ እርሱ የሚናገረው እንደ ንጉሥ ነው።

እውነቱ፡- የተናገርኸው እውነት እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ፤ እርሱ ታላቅ ንጉሥ፥ የነገሥታት ንጉሥ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር «እኛ» እያለ በሚናገርበት ጊዜ ከታላቅነት የበለጠ ነገር አያመለክትም ይሆን?

አህመድ፡- አሁን የሥላሴን አሳብ ልታመጣ እየሞከርህ እንደሆነ ይታየኛል።

እውነቱ፡- እስኪ የእግዚአብሔርን ምሥጢር ላሳይህ ልሞክር። በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ በመጥምቁ ዮሐንስ እንደ ተጠመቀ የሚናገር ታሪክ አለ። እንደሚከተለው ይነበባል።

«ዮሐንስ ግን፡- እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር። ኢየሱስም መልሶ፡- አሁንስ ፍቀድልኝ፥ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው... ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም፥ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም፥ ድምፅ ከሰማያት ወጥቶ፡- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ» (ማቴዎስ 3፡14-17)።

እነዚህ ቁጥሮች «የምወደው ልጄ» ያለውን እግዚአብሔር አብን፥እግዚአብሔር ወልድንና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ሦስቱንም በአንድ ላይ ያሳዩናል። ከሰማይ ድምፅ የመጣ ሲሆን፥ ርግብ የሚመስልና ነገር ግን ርግብ ያልሆነ ነገር ከሰማይ ወርዷል፤ ኢየሱስም ከውኃው ሲወጣ ነበር።

አህመድ፡- ግን ይህ መንፈስ ቅዱስ የተባለው ነገር እንደ ርግብ በእርሱ ላይ መውረዱ አምላክ የሚያደርገው አይመስለኝም። ደግሞስ መጽሐፋችሁ መጥምቁ ዮሐንስ ገና ሳይወለድ በእናቱ ማኅፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞላ ይናገር የለ? ስለዚህ ዮሐንስ ከኢየሱስ አይበልጥም ነበር ወይ? ወይስ ዮሐንስና ኢየሱስ አምላኮች ነበሩ ማለት ነው?

እውነቱ፡- እኔ ይህንን ጥቅስ ያነበብሁልህ ክርስቲያኖች ኢየሱስን እንደ አምላክ የሚቀበሉበትን ምክንያት ለማሳየት አይደለም። መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ መውረዱ ኢየሱስን አምላክ አያደርገውም ማለትህ ትክክል ነው። ይህንን ታሪክ የተጠቀምሁት፥ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአንድ ጊዜ መገኘታቸውን ላሳይህ ፈልጌ ነው። አንዱ በሰማይ፥ አንዱ በምድር፥ ሌላው በሰማይና በምድር

መካከል ሲበር ታያለህ። እነዚህ ሦስት አካላት ሲሆኑ፥ መጽሐፍ ቅዱሳችን እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አበክሮ ያስተምራል (ዘዳግም 6፡4፤ ማርቆስ 12፡29)።

አህመድ፡- አሁንም ለማለት የምችለው ነገር ቢኖር መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ስለዚህ ታሪክ የሚናገረው ነገር የተሳሳተ መሆኑን ብቻ ነው። የእናንተ መጽሐፍ ቅዱስ ከእኛ ቁርአን የተለየ ነው። ብዙ መዛግብቶች ያሉአችሁ ሲሆን፥ በዚያው ልክ ብዙ ለውጦችን ታደርጋላችሁ። እኛ ግን ቁርአናችንን ለውጠን አናውቅም። አንዱ ከሌላው የሚለያይ ምንም መዛግብት የሉንም።

እውነቱ፡- አሁንም የተናገርኸው ትክክል ነው። እኛ በርካታ ጥንታዊ የብሉይና የአዲስ ኪዳን መዛግብቶች አሉን። እናንተ ግን አንድ ቁርአን ብቻ ነው ያላችሁ። ለምን ግን አንድ የቁርአን መጽሐፍ ብቻ ሊኖራችሁ እንደ ቻለ ታውቃለህ?

አህመድ፡- ምክንያቱም የእኛ ቁርአን በቀጥታ ከአላህ ዘንድ በመልእክተኛው በገብርኤል አማካኝነት ለነቢዩ መሐመድ መጥቶ ስለ ተጻፈልን ነው።

እውነቱ፡- ቁርአን በሙሉ እንዲሰባሰብ ያዘዘው ካሊፍ ኡስማን ሲሆን፥ ይህንኑ ታላቅ ተግባር ያከናወነው ዛይድ ነበር፤ ይኼ እውነት አይደል? (ሳሂህ አል-ቡክሃሪ)፥ ጥራዝ 4፥ ገጽ 466 እና ጥራዝ 6፥ ገጽ 477)።

አህመድ፡- አዎን፥ ታሪካችን የሚናገረው ይህንኑ ነው።

እውነቱ፡- ዛይድ ተግባሩን አከናውኖ ሲያበቃ፥ እርሱ ከሰበሰባቸው መዛግብት ጋር የሚጋጩ መጻሕፍት ሁሉ ምን ተደረጉ?

አህመድ፡- ዛይድ ከሰበሰበው የሚጋጩ መዛግብት መኖራቸውን አላውቅም።

እውነቱ፡- የሚጋጩ መዛግብት ነበሩ። ስለሆነም፥ ኡስማን አንድ ቁርአን ብቻ እንዲኖር እነዚህን መዛግብት ያጠፉአቸው ዘንድ አዘዘ (ሳሂህ አል-ቡክሃሪ፥ ጥራዝ 6፥ ገጽ 479)። አየህ፥ እኛም ክርስቲያኖች አንድ መዝገብ ብቻ እንዲኖረን ልናደርግ እንችል ነበር። አንዱን መዝገብ፥ እንበልና ታላቁን ኮዲክስ ቫቲካነስ ብቻ አስቀርተን ሌሎቹን ልናጠፋ እንችል ነበር። ይህን ብናደርግ ኖሮ ግን

ትክክለኛውን መዝገብ ስለ መምረጣችን እርግጠኞች ልንሆን አንችልም ነበር። ክርስቲያን ምሁራን አንዱን መዝገብ ከሌላው ጋር አወዳድረው ሙሉ ለሙሉ የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን ሊሰጡን ችለዋል። ለምሳሌ፥ አንድ ሰው ዮሐንስ 1፡1 "THEOU" ወይስ "THEOS" መሆን እንዳለበት ቢሞግት ሁለት ሺህ መዛግብት አቅርበንለት ከመካከላቸው አንድ እንኳ "THEOU" የሚል እንዳለ እንዲመለከት ልንጠይቀው እንችላለን።

አህመድ፡- መዛግብቱን ሁሉ ማስቀመጥ አንዳንድ ጥቅሞች እንዳሉት ልረዳ ችያለሁ። አሁን በእጅ ካለው የሚለዩ የቁርአን ቅጂዎች አሉ?

እውነቱ፡- ቁርአን መጀመሪያ የተጻፈው በዐረብኛ እንደሆነ ታውቃለህ፤ ይህም የድሮ የቁርአን ጽሕፈት አናባቢ ፊደላት አልነበሩትም፤ በመሆኑም፥ አናባቢዎች በሚጨመሩበት ጊዜ በአንዳንድ ስፍራዎች የትኞቹ አናባቢዎች መግባት እንዳለባቸው ምሁራን በአሳብ ተለያዩ። እንዲሁም ደግሞ የተለየ በመሆኑ ከኡስማን በኋላ ቢያንስ ለሦስት መቶ ዓመታት የኖረ አንድ የቁርአን ስብስብ ነበር (እብን አቢ ዳውድ፥ <u>ኪታብ አል-ማሳሂፍ</u>፥ ገጽ 13-15፥17 እና አስ-ሱዩቲ፥ <u>አል ኢታቃን ፊ ሁላም አል-ቁርአን</u>፥ ገጽ 150 152-154 ተመልከት)። አሁን ግን ጠፍቶአል።

አህመድ፡- አዲስ ኪዳን ስለ መሐመድ መምጣት መተንበዩ እውነት ነውን? ስለ ትንቢቱ ተዛማጅነት በትክክል የማውቀው ነገር የለኝም።

እውነቱ፡- አንተ የምትለው ትንቢት የትኛው እንደሆነ የተረዳሁት ይመስለኛል። ይህ የሚገኘው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ «ጰራቅሊጦስ» ለመላክ ቃል በገባበት በዮሐንስ 16፡7 ነው። «እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፥ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ (ጰራቅሊጦስ) ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልከላችኋለሁ።»

አህመድ፡- አዎ፥ ትንቢቱ ያ ነው። «ጰራቅሊጦስ» የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙም «የተባረከ» ማለት ነው፤ አይደል? የመሐመድም ስም የተባረከ ማለት ነው።

እውነቱ፡- ከተናገርኸው ግማሹ እውነት ነው። «ጰራቅሊጦስ» የሚለው ቃል ግሪክ መሆኑ ቢታወቅም፥ ትርጉሙ ግን የተባረከ ማለት አይደለም። «ጰራቅሊጦስ» ማለት ረዳት፥ አጽናኝ፥ መካሪ፥ በችሎት ፊት የሚቆም ጠበቃ ማለትም በጥፋት ለተከሰሰ ሰው ተከላካይ ሆኖ የሚቆም ነው።

አህመድ፡- ነገር ግን ተስፋ የተገባለት ጰራቅሊጦስ የተባረከው መሐመድ እንደሆነ ብዙ ጊዜ ሰምቻለሁ።

እውነቱ፡- ብዙ መዛግብት መኖሩ የሚጠቅመው ለዚህ ነው። አንድ ሰው በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተጻፈውን ጰራቅሊጦስ ማለትም አጽናኝ «ፐሪክሊቶስ» ከተባለና የተባረከ የሚል ፍች ከሚሰጠው የግሪክ ቃል ጋር አምታታ። ነገር ግን ባሉን በመቶዎች በሚቆጠሩ የአዲስ ኪዳን መዛግብት ውስጥ አንድም «ፐሪክሊቶስ» የሚል አይገኝም፤ ሁሉም ጰራቅሊጦስ የሚሉ ናቸው።

አህመድ፡- አንተ እንደምትለው፥ መጽሐፍ ቅዱስ የመሐመድን መምጣት የማይተነብይ ከሆነ፥ ጰራቅሊጦስ የተባለው እንግዲህ ማንነው?

እውነቱ፡- በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የሚገኝ ሌላ ጥቅስ ይህን ኢየሱስ ለሐዋርያት ያለውን በግልጽ ያብራራዋል። «ከእናንተ ዘንድ ስኖር ይህን ነግሬአችኋለሁ፤ አብ በስሜ የሚልከው ግን «ጰራቅሊጦስ» የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል (ዮሐንስ 14፡25-26)።

አህመድ፡- እንግዲህ፥ ጰራቅሊጦስ የእናንተ ሥላሴ ሦስተኛ አካል የሆነው መንፈስ ቅዱስ መሆኑ ነው።

እውነቱ፡- ‹ሥላሴ› የሚለውን ቃል ገና አልተጠቀምሁም። ነገር ግን በዚሁ በዮሐንስ ወንጌል ኢየሱስ ለሐዋርያት የሚከተለውን ብሏል።

«እኔም አብን እለምናለሁ፤ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ «ጰራቅሊጦስ» ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይችለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ» (ዮሐንስ 14፡16-17)።

ስለሆነም፥ ይህ ጰራቅሊጦስ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ከአብ ጋር በሰማይ የሚኖር ነው፤ እርሱም የሚሞት የሰው ልጅ ሳይሆን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለዘላለም የሚኖር የእውነት መንፈስ ነው።

እንዲሁም ኢየሱስ ሐዋርያቱን ወደ ዓለም በላካቸው ጊዜ አዳዲስ ክርስቲያኖችን «በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም» እንዲያጠምቁ መናገሩ አስገራሚ ነገር ነው (ማቴዎስ 28፡18–20)። በሌላም ስፍራ ሦስቱ በአንድ ላይ ተጠቅሰው እናገኛለን። «የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን» (2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14)

አህመድ፡– አሁን የተረዳሁት፥ መጽሐፍ ቅዱስን በምታጠናበት ጊዜ እግዚአብሔር አንድ እንደሆነና ዳሩ ግን ያው አንድ አምላክ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ የሚያመለክት አሳብ እንዳገኘህ ነው።

እውነቱ፡– እስካሁን ግን በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን መካከል ስለሚገኘው እጅግ አስፈላጊ ልዩነት አልተነጋገርንም። መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳት መጻሕፍት፥ ‹የሙሴ ሕግ፥ ነቢያትና መዝሙራት› እንደሚሉት፥ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንደሞተ ይናገራል (ሉቃስ 24፡44–47፤ የሐዋርያት ሥራ 2፡22–23፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡3–4፤ ፊልጵስዩስ 2፡5–8፤ ቈላስይስ 1፡19–22)፤ ቁርአን ግን በሴቶች ሱረቱ ውስጥ አይሁዶች ኢየሱስን አልገደሉትም አልሰቀሉትም ነው የሚለው (ሱረቱ 4፡157)።

አህመድ፡– በእርግጥ በእኛ በሙስሊሞች መካከል በዚህ ሱረት አተረጓጎም ላይ የአሳብ ልዩነት አለ፤ ይህም ሆኖ፥ ሁላችንም ሙስሊሞች ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንዳልሞተ እናምናለን።

እውነቱ፡– አህመዳውያን እንደሚሉት፥ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ ግን አልሞተም፤ ገና ነፍሱ ሳትወጣ ከመስቀሉ አውርደው ቀበሩት። ሌሎች ሙስሊሞች ደግሞ ኢየሱስ በጭራሽ እንዳልተሰቀለ ያምናሉ። ያ ትክክል ነው?

አህመድ፡– አዎ፥ ያ ትክክል ነው። አህመዳውያንን ግን እንደ እውነተኛ ሙስሊሞች የሚቆጥራቸው የለም።

እውነቱ፡– የእነርሱን ክርክር መመለሱ ቀለል ይላል። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን ከመስቀሉ አውርደው በሚወስዱት ጊዜ፥ ገና እንዳልሞተ ይናገራሉ፤ ነገር ግን በቦታው ሆነው የሰቀሉት

የሮም ወታደሮች መሞቱን ተረድተው ነበር፤ ለዚህም ነው ሰው ቶሎ እንዲሞት የሚያደርጉትን የእግር ሰበራ ተግባር በእርሱ ላይ ያልፈጸሙት (ዮሐንስ 19:30-37)። የወታደሮች አዛዥ የነበረው መቶ አለቃ በመስቀሉ ላይ ከተሰቀለው ከኢየሱስ ፊት ለፊት ቆሞ ይህንኑ እውነት ተመልክቷል (ማርቆስ 15:39)። ስለሆነም፥ የአርማትያው ዮሴፍ የኢየሱስን ሥጋ ለመቅበር ጲላጦስን በጠየቀ ጊዜ የሚከተለውን ምላሽ እንዳገኘ እናነባለን፤ «ጲላጦስም አሁኑኑ እንዴት ሞተ ብሎ ተደነቀ፥ የመቶ አለቃውንም ጠርቶ ከሞተ ቆይቷልን? ብሎ ጠየቀው፤ ከመቶ አለቃውም ተረድቶ በድኑን ለዮሴፍ ሰጠው» (ማርቆስ 15:44-45)።

አህመድ፡- አህመዳውያን ስለ ኢየሱስ የከፈን ጨርቅ በማንሣት፥ ከመስቀሉ በወረደ ጊዜ ሕያው እንደነበረ ያረጋግጣል ይሉ ነበር፤ አሁን ግን ስለዚህ ጉዳይ አይናገሩም። ለምን?

እውነቱ፡- የከፈን ጨርቁ ክርስቶስ ሲቀበር ሰውነቱ የተሸፈነበት እንደሆነ በአንዳንድ ሰዎች ይታመን ነበር። አህመዳውያን በዚያው ጨርቅ ላይ የሚገኙ የደም ምልክቶች በጨርቁ የተጠቀለለው ሰውዬ እንዳልሞተ የሚያመለክቱ መሆናቸውን ተናገሩ።

አህመድ፡- ያ በጣም አስገራሚ ነገር ነው። እንግዲህ አሁን ስለዚህ ጉዳይ አይነጋገሩም ማለት ነው?

እውነቱ፡- አሁን ጉዳዩን የማያነሡት የከፈን ጨርቁን ጠብቃ ያኖረችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሳይንቲስቶች የጨርቁን ዕድሜ እንዲመረምሩ ስላደረገች ነው። ምርመራውም ጨርቁ የተገኘው ከክርስቶስ ሞት በኋላ አምስት መቶ ዓመታት ዘግይቶ እንደነበር አመልክቷል!

አህመድ፡- አብዛኞቹ ሙስሊሞች የኢየሱስን መስቀል አያምኑም፤ ለዚህም ምክንያቱ የቁርአን ቃል ነው፤ «አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትም» (ሱረቱ 4:157 የሴቶች ምዕራፍ)።

እውነቱ፡- አዎ፥ ክርስትናና እስልምና በአንድነት ሊቆሙ የማይችሉበት አንዱ ነጥብ ይኼ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ቁርአን ትክክል ነው። ክርስትና ወይም እስልምና ትክክል ነው። ሁለቱንም ትክክል የምናደርገበት መንገድ የለም።

የክርስቶስን መሰቀል ወይም አለመሰቀል እንሥተን ብንከራከር ማናችንም አናሸንፍም። እኛ ተሰቅሏል ስንል እናንተ አልተሰቀለም ትላላችሁ። እዚያም ላይ ጨምራችሁ በእርሱ ምትክ አንድ ሌላ ሰው እንደ ተሰቀለ ትናገራላችሁ፤ ይህ እውነት አይደለም?

አህመድ:- እውነት ነው፤ የበርናባስ ወንጌል እንደሚለው፥ የተሰቀለው የአስቆሮቱ ይሁዳ ነው። የበርናባስ ወንጌልም በጣም አስፈላጊ ነው። በርናባስ እውነተኛውን ወንጌል ይነግረናል፤ ኢየሱስ በተያዘ ጊዜ የተፈጸመውን ነገር በትክክል ይገልጽልናል።

እውነቱ:- እዚህ ላይ የበርናባስ ወንጌል የሚሰጥህ እገዛ አይኖርም። ይህ በእርሱ ወንጌል የተባለው ነገር በበርናባስ የተጻፈ አይደለም፤ በመጀመሪያው ምእተ ዓመትም አልተዘጋጀም ነበር፤ በግሪክ ወይም በዕብራይስጥ ወይም በዓረብኛ የተጻፈም አይደለም። ይህ ከመሐመድ ዘመን በኋላ፥ አባ ሞሬኖ በተባለ የሮም ካቶሊክ ቄስ አማካኝነት የተደረሰ ነው፤ ይህ የሆነው ሰውዬው ወደ እስልምና ሃይማኖት ከገባ በኋላ ሲሆን፥ የተጻፈውም በጣልያንኛ ነው።

አህመድ:- ይኼን ማመን ይቸግረኛል። ሁሉም ሙስሊሞች ማለት ይቻላል የበርናባስ ወንጌል የጳውሎስ ጓደኛ በነበረው በበርናባስ የተጻፈ እውነተኛው ወንጌል እንደሆነ ያምናሉ።

እውነቱ:- አዎ፥ ግን የበርናባስ ወንጌል ከቁርአን ጋር በአያሌ መንገዶች እንደሚጋጭ አታውቅ ይሆናል። የበርናባስ ወንጌል ማርያም ኢየሱስን ያለ ምንም የምጥ ጣር እንደ ወለደችው ሲናገር (በርናባስ 3)፥ ቁርአን ግን ማርያም ኢየሱስን ስትወልድ ምጥ እንደ ያዛት በግልጽ ይናገራል (ሱረቱ 19:22-23)። ከዚህም በላይ ይህ የበርናባስ ወንጌል የተባለው መጽሐፍ ኢየሱስ መሢሕ አይደለሁም ብሎ አራት ጊዜ እንደ ካደ ይናገራል (በርናባስ 42፥82፥ 96፥ 198)። ቁርአን ግን ኢየሱስን ቢያንስ ዘጠኝ ጊዜ መሢሕ እያለ ጠርቶታል (ሱረቱ 3:45፤ 4:157፥ 171፥ 172፥ 5:17፥ 72፥ 75፤ 9:30-31)።

ስለሆነም፥ ከቁርአንና ከበርናባስ ወንጌል አንዱን ሥልጣን እንዳለው አድርገህ መምረጥ እንዳለብህ ልትገነዘብ ይገባል፤ መቼም እንደ ሙስሊም ከበርናባስ ወንጌል ይልቅ ቁርአንን እንደምትመርጥ ነው የማምነው። አሁንም ቢሆን ይሁዳ በኢየሱስ ምትክ እንደ ተሰቀለ

የምታምን ከሆነ፥ ሌላ የተሻለ መረጃ መፈለግ ይኖርብሃል። ለዚህ መረጃነት የበርናባስን ወንጌል ልትጠቀም አትችልም።

አህመድ፡- የበርናባስ ወንጌል ውድቅ ቢሆን እንኳ፥ በቁርአን ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ የሚናገር ኢየሱስ አልተሰቀለም የሚል ቃል አለን፤ እንዲሁም ቁርአን የተሰጠን በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ የሚገኙትን ሕግ፥ መዝሙራትና ወንጌላት ለማረም እንደሆነ ሰምቻለሁ። የእናንተ ቅዱሳት መጻሕፍት ተበርዘው ተበላሽተዋል።

እውነቱ፡- ብዙ ጥንታዊ መዛግብት መኖራቸው የሚረዳው እዚህ ላይ ነው፤ ከእነዚህም መዛግብቶች አንዳንዶቹ ከመሐመድ ዘመን በፊት የተጻፉ ናቸው። ስለሆነም፥ እነዚህን ብዙ መዛግብት ዛሬ ካሉት በርካታ የቋንቋ ትርጉሞች ጋር በማስተያየት፥ በውስጣቸው የነበረው ቃል ዛሬ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ከምንጠቀምበት ጋር አንድ መሆኑን ማመሳከር ይቻላል፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራዎች ከመሐመድ ዘመን በፊት የተከናወኑ ጥቂቶች እንዳሉም ግልጽ ነው።

ሌላም ጥያቄ አለኝ፤ ቶራ፥ ዛቡር (መዝሙራት) እና ኢንጅል (ወንጌላት) የተበረዙት መቼ ነበር? ይህ ከመሐመድ ዘመን በፊት መሆን ነበረበት። ይህ ከሆነ፥ ቁርአን እነዚህ ጽሑፎች ለሰው ልጆች «መመሪያና ብርሃን» ይሆኑ ዘንድ በአላህ መላካቸውን የሚናገረው ለምንድን ነው? (ሱረቱ 5፡44)። ክርስቲያኖችና አይሁዶች አላህ በእነዚያ መጻሕፍት ከገለጠው እውነት አኳያ እንዲፈርዱ የተነገራቸው ለምንድን ነው? (ሱረቱ 5፡47)። መጽሐፍ ቅዱስስ ሰዎች የሚቆሙበት ብቸኛ መሠረትና ከጌታ ዘንድ የመጣ መገለጥ ተብሎ የተጠቀሰው ለምንድን ነው? (ሱረቱ 5፡68)። ሙስሊሞች፥ «ለሙሳና ለዒሳም፥ ለነቢያትም ሁሉ ከጌታቸው በተሰጠው (አመንን)!» ብለው የእምነት መግለጫ መስጠት የሚኖርባቸው ለምንድን ነው? (ሱረቱ 3፡84)። አላህ እነዚህ መጻሕፍት ሁሉ የተበላሹ መሆናቸውን ማወቁ አይቀርም ነበር፤ ይህ ከሆነ፥ እነዚህን ትእዛዛት በቁርአን ውስጥ ለአይሁዶች፥ ለክርስቲያኖችና ለሙስሊሞች የሰጠው ለምንድን ነው?

አህመድ፡- ምናልባትም መጽሐፎቻችሁ አልተበላሹም ይሆናል፤ ነገር ግን እኛ ሙስሊሞች ኢየሱስን ስናከብር እናንተ ግን እንደ ተዋረደ፥ እንደ ተሠቃየና ከዚያም አልፎ በእግዚአብሔር ፈቃድ የከፋ ሞት እንደ ሞተ በመናገር ታዋርዱታላችሁ።

እውነቱ፡- አብዛኞቹ ሙስሊሞች በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞት መርገም እንደ መሆኑ፥ እግዚአብሔር እንደ እርሱ ያለ

ነቢይ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ እንዲሞት አያደርግም ብለው እንደሚያስቡ ግልጽ ነው። እንደዚህ ነው የምትሉት አይደል?

አህመድ፡- አዎ፥ እንደዚህ ነው የምንለው፤ እኔም የማምነው ይህንኑ ነው።

እውነቱ፡- ይህ ምንም እንኳ አንተን ሊያስገርምህ ቢችልም፥ የኢየሱስ ሞት የመርገም ሞት እንደሆነና የመርገም ሞትም መሆን እንደነበረበት አምናለሁ፤ ይህም እግዚአብሔር በመረጠውና ከመጀመሪያው በወጠነው ዕቅድ መሠረት የተፈጸመ ነው (ዘዳግ. 21፡22–23፤ ኢሳይያስ 53፡4–12፤ ገላትያ 3፡10–13)። ኢየሱስ «አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ?» ሲል የጮኸውም ለዚሁ ነው (ማርቆስ 15፡34)። በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የዓለሙን ሁሉ ኃጢአት እየተሸከመ ነበር፤ በዘመናት ሁሉ ሰዎች የፈጸሟቸውን ኃጢአቶች ሁሉ ዋጋ እየከፈለ ነበር (ሮሜ 3፡23–26፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)።

አህመድ፡- ግን እኮ ማንም ሰው የሌላውን ሰው ኃጢአት ዋጋ ሊከፍል አይችልም።

እውነቱ፡- በእርግጥ ማንም ሰው የሌላውን የኃጢአት ዋጋ ሊከፍል አይችልም፤ ኢየሱስ ግን ሰው ብቻ አልነበረም። እርሱ ሥጋ የለበሰ አምላክ ነበር (ማቴዎስ 1፡22–23፤ ቈላስይስ 1፡15–19፤ ዕብራውያን 1፡3) እርሱ ሊያደርግ ከፈለገ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ይኖር ይሆን?

አህመድ፡- የለ ለአምላክ የሚሳነው ነገር የለም።

እውነቱ፡- ኢየሱስ፥ «አባ አባት ሆይ፥ ሁሉ ይቻልሃል፤ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን አንተ የምትወደው እንጂ እኔ የምወደው አይሁን» ሲል ጸልዮአል (ማርቆስ 14፡36)።

አህመድ፡- አሃ...ኢየሱስ እነዚያን የመጨረሻ ቃላት እንደተናገረ አላውቅም ነበር፤ «እኔ የምወደው አይሁን...»

እውነቱ፡- አንዳንድ ሙስሊም ደራሲያን እነዚያን ቃላት ሆን ብለው በመተው ሕዝቡ ኢየሱስ ከሞት ለማምለጥ ስለ ጸለየ እንደ ነቢይነቱ ጸሎቱ ሳይመለስ አይቀርም ብሎ እንዲያስብ ማድረጋቸው የሚያሳዝን ነው። እውነቱ ግን እነርሱ እንዳሰቡት አይደለም፤ ጸሎቱ ተመልሶ የአባቱ ፈቃድ

ተፈጽሟል (1ኛ ዮሐንስ 2:2)። በመስቀል ላይ የሞተው እርሱ እንጂ ይሁዳ አይደለም። ለእግዚአብሔር በስሕተት በአንደኛው ሰው ምትክ ሌላውን በእንዲህ ዓይነት ሞት መቅጣቱ የከፋ ነገር ነው የሚሆነው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት የተቀበረ ሲሆን፥ በሦስተኛው ቀን ተነሥቶ ወደ ሰማይ ዐርጓል። አሁንም ያለው እዚያው ነው።

አህመድ፦ በነገርኸኝ ነገር ላይ በጥብቅ እንደማስብበት ልገልጽልህ እፈልጋለሁ።

እውነቱ፦ አብረን መነጋገራችን በጣም ጥሩ ነበር። እግዚአብሔር ሁለታችንም የእርሱን እውነት በጥልቅ እንረዳ ዘንድ እንዲመራን እጸልያለሁ። እግዚአብሔር ይባርክህ፥ የእኔ ወንድም።

አህመድ፦ ደህና ዋል!